# የፀረ-ሙስና ወንጀል ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ተግባርና ኃላፊነት

- የምርመራና የክስ ስራዎች ውጤታማ እንዲሆኑ ያስተባብራል፣ ይከታተላል፣ ይደግፋል፣ ይመራል፤
- ጥቆማዎችና የጥቆማ ሰጪዎችን ማንነት በሚስጢር ለመያዝ የሚያስችል አሰራር ይዘረጋል፣አፈጻጸማቸውን ይከታተልል፣ ይቆጣጠራል፤
- በቀረቡ አቤቱታዎችን ላይ ምላሽ ይሰጣል፤ ምላሽ እንዲሰጥ ያደርጋል፤ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፤
- የክልሉን መንግሥት በመወከል ወይም በፌደራል በተሠጠው ውክልና መሰረት በወንጀል ጉዳዮች ክስ ይመሰርታል፤ በወንጀል የሚያስጠይቅ ሁኔታ መኖሩ በግልፅ ሲታወቅ የወንጀል ምርመራ እንዲቋረጥ ወይም የተቋረጠ የወንጀል ምርመራ እንዲቀጥል ትዕዛዝ ይሰጣል፤ በቂ ማስረጃ ካልተገኘ በህግ አግባብ የክስ አይቀርብም ውሳኔ ይሰጣል፤የክስ ይነሳልኝ አቤቱታዎችን ተቀብሎ ተገቢውን ውሳኔ ይሰጣል፤
- በወንጀል የተገኘ ጥቅም እንዲመለስ በማድረግ በሙስና ወንጀል ክስ የተመሰረተባቸው ወይም በምርመራ ሂደት ላይ ያሉ ወይም የምርመራ ሂደታቸው ተጠናቆ ለውሳኔ የደረሱ የሙስና ወንጀል መዛግብትን ከክስ በመለስ እንዲቋጩ ያደርጋል፤
- በዞን የሙስና ወንጀል ጉዳዮች የሥራ ሂደት ውሳኔ አግባብነት በመመርመር ውሳኔውን ይሽራል፣ያሻሽላል፣ያፀናል፤
- በአግባቡ መያዝ የሚገባቸውን ማስረጃ ባልያዙ መዛግብት ላይ ተገቢውነ ማስረጃ እንዲይዙ ተጨማሪ ነጥቦችን በማውጣት እንዲያሟሉ ለፖሊስ ትዕዛዝ ይሰጣል፤
- በወንጀል መዛግብት ላይ የተሠጡ የዓቃቤ -ህግና የፍርድ ቤት ውሳኔዎችን ለሚመለከተው አካል ያሳውቃል፤
- በህግ መሰረት የጥፋተኝነት ድርድር ያደርጋል፤ አማራጭ የመፍትሄ እርምጃ ይወስዳል፤ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤
- በህግ መሰረት ቀዳሚ ምርመራ እንዲከናወን ያደርጋል፤
- የእጅ ተፍንጅ ወንጀሎች ተፈፅመው ሲገኙ በተፋጠነ ሥነ-ሥርዓት ውሳኔ የሚያገኙበትን መንገድ ያመቻቻል፤ ለዚህም ከፖሊስና ከሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተባብሮ ይሰራል፤
- በሙስና ወንጀል ጉዳይ ሚቀርቡ ምስክሮች በወቅቱ መጥሪያ እንዲያደርስና ምስክሮችን ፍርድ ቤት እንዲያቀርብ ለፖሊስ ትዕዛዝ ይሰጣል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የዐቃቤ ህግ ምስክሮች ተገቢውን ጥበቃ እንዲያገኙ ያደርጋል፤
- ፍርድ ቤቶች በወንጀል ጉዳይ የሚሰጧቸው ውሳኔዎችና ትዕዛዞች መፈፀማቸውንና መከበራቸውን ይከታተላል፤አፈፃፀማቸው ሕግን ያልተከተለ ከሆነም በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ለሰጠው ፍ/ቤት በማመልከት የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

- ከፍርድ ቤት የሚላኩ የወንጀል መቀጮዎችን፣ የዋስትና ገንዘቦችንና እንዲወረሱ የተባሉ ንብረቶችን ለመንግስት ገቢ ያስደርጋል፤
- ከወንጀል መዝገቡ ተነጥለው መታየት ያለባቸው ፍትሐብሔራዊ ክርክሮች ሲያጋጥሙ ለሚመለከተው የስራ ክፍል ከሙሉ መረጃ ጋር ያስተላልፋል፤
- ክስ በቀረበባቸው ጉዳዮች ላይ ምስክሮች የሚያስረዱትን ተገንዝቦ፣ የክርክር ፍሬ ነገሮችን ከቀጠሮው በፊት አጥንቶና ተዘጋጅቶ በመቅረብ ይከራከራል፤ አስጠቂ በሆኑ ምስክሮች ላይ ምርመራ እንዲካሄድ ያዝዛል፤ ውጤቱን ይከታተላል፤
- ከሙስና ወንጀል ባህሪ አኳያ ውስብስብ ጉዳዮች ሲያገጥሙ ምርመራውን ከፖሊስ ጋር በቡድን ያከናውናል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤በአጠቃላይ ምርመራን በበላይነት ይመራል፤
- በተጠርጣሪዎች የሚቀርብ የዋስትና መብት ይከበርልኝ፣ በዋሶች የሚቀርብ ዋስትና ይነሳልኝ ወይም በዋስትና የተያዘ ንብረት ይለቀቅልኝ የሚል አቤቱታ ለፍ/ቤት ቀርቦ መልስ እንዲያቀርብ ሲታዘዝ መልስ በማቅረብ ክርክር ያደርጋል፤
- ከተጠረጠሩ ሰዎች በኤግዚቢትነት የተያዙ ንብረቶች አፋጣኝ ውሳኔ እንዲያገኙ ያደርጋል አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፤
- የሙስና ወንጀሎችን ለመከላከልና ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችሉ ጥናቶችን ያደርጋል፤የስራ ክፍሉ ለማሻሻል የሚረዱ የስልጠና ፅሁፎችን ያዘጋጃል ስልጠና ይሰጣል፤
- የይግባኝና የሰበር አቤቱታ ማቅረብ እና ምላሽ መስጠት፤
- ውስብስብ በሆኑ የወንጀል መዛግብት እና ከስር ዐቃቤያነ ህግ በሚቀርቡ የመሪ ትዕዛዝ ጥያቄዎች ላይ መመሪያ ይሰጣል አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፤
- በወንጀል ጠቋሚዎችና ምስክሮች የህግ ከለላ የሚሰጥበትን ሁኔታ ከወንጀል ጉዳዮች ምክትል ቢሮ ኃላፊ ጋር በመመካከር ያመቻቻል፣ ይከታተላል፤ይተገብራል የተወሰደ የበቀል እርምጃ ካለ በህግ አግባብ ያግዳል ያጣራል አፈፃፀሙን ይከተተላል፤
- ከሙስና ወንጀል ጉዳዮች ጋር በተየያዘ ከቢሮ ኃላፊው እና የዘርፉ ምክትል ቢሮ ኃላፊ ተለይተው የሚሠጡ ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፤
- በስውር የሙስና ወንጀል መረጃ የሚሰበሰብባቸውን አካላት ከቢሮ ኃላፊው እና ዘርፉን ከሚመራው ምክትል ቢሮ ኃላፊው ጋር ሆኖ ይለያል፤
- ወደ ምስክር የሚዞሩ ተጠርጣሪዎችን ቃል በመገምገም በየደረጃው ያለው የበላይ አመራር ሲወሰን ቃል እንዲሰጡ ያደርጋል፤
- የሙስና ወንጀል ተጠርጣዎችን የስልክ፣ የፖስታና ሌሎች ሚስጥራዊ ግንኙነት እንዲጠለፍ ለቢሮ ኃላፊው የውሳኔ ሃሳብ ያስቀርባል አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

- በሙስና ወንጀል የተጠረጠሩ ባለስልጣናን እና ያለመከሰስ መብት ያላቸው ተጠርጣሪዎችን የወንጀል ተሳትፎ ይለያል፤ በየደረጃው ባለው የበላይ አመራር ሲወሰን ቃል እንዲሰጡ ያደርጋል፤
- በሙስና ወንጀል የተጠረጠሩ ሰዎችን ሀብት እንዲጣራ ያደርጋል፤
- የፀ-ሙስና ትግሉን ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችሉ ጥናቶችን ያደርጋል አዳዲስ የአሰራር ስርዓቶችን ይዘረጋል፤
- በሙስና ወንጀል እና ሰብአዊ መብት ላይ የግንዛቤ ፈጠራ ሥራ (ንቃተ-ህግ ሥራ መስራት)
- ቅድመ ክስ ክርክር ማድረግ፤
- በአጠቃላይ በአዋጅ ቁጥር 433/1997፣434/1997፣አዋጅ ቁጥር 881/2007፣አዋጅ ቁጥር 882/2007 ፣አዋጅ ቁጥር 883/2007፣ዝክረ-ህግ 237/2008፣ዝክረ-ህግ 263/2011 እና ዝክረ-ህግ 280/2014 ላይ የተቀመጡ ተግባር እና ኃላፊነት በአግባቡ ያከናውናል፤